# <u>የትግልም የሀገርም ባለቤት ሕዝብ እንጂ ምርጦች አይደሉም፡፡</u>

ሀማ ቱማ

“አይገኝም ከቶ ቢፈልጉ ዞሮ
መስማት ከማይፈልግ የባሰ ደንቆሮ
አጊጦ ሲያምርበት ዕውቀት በትሕትና
ኩራት አስጠየፈ ለብሶ ድንቁርና”

ከበደ ሚካዔል/ ብርሀነ ኅሊና/

ሞኝ መካሪውን አይወድም እንዲሉ ዛፍ ተቆርጦ ባላለቀበት እምቧጮ አይሞሸርብን በሚል መንፈስ በህዝብ ትግል ላይ አወቁ አላወቁ ግን ሁሌም አወቅን ብለው በደል የሚፈፅሙትን ግለሰቦች ሆኑ የድርጅት መሪዎች እባካችሁ ጠንቀቅ እንበል አደብ እንግዛ ብዬ የአቅሜን ልመክር ብነሳ በዚህም በዚያም ያው እንደጠበቅኩት ውርጅብኙ ተዥጎድጉዷል፡፡ በፈረንጅ ዕውቀት ተኩራርቶ መገኘቱና ይባስ ብሎ ህዝብን መናቁ በድንቁርና ያስፈርጃል በማለቴም የተማሩትን ወቀሰ በሚልም ሊያወግዙኝ የሞከሩ ብቅ ብለዋል፡፡ ከቃለ አጋኖ ተቆጥበን ሁኔታን እንመርምር ያልኩትንም ቢሆን ከላይ የጠቀስኳቸው አቶ ከበደ ሚካዔል ድሮ ድሮ

“ምን ውብ ነገር ቢሆን ከማድነቅ በፊት
ይገባል ጭራሹን ቀድሞ መመልከት”

ብለው የፃፉት ቢሆንም ጣዖት ጠራቢዎቹ ስራ አሳጣኸን በሚል መንፈስ ክሱን ደርድረውብኛል፡፡

በዚህም በዘያም ግን ምነው ጩኸት በረከተ ብለን ብንጠይቅ ከባዕድ ለስላሳ የራስ ከርካሳ መባሉ ይህን ያህል ሊያስቆጣ ባልተገባ ነበር፡፡ ቆዳ ለማንጣት ተብሎ የካንሰር በሽታን እስከመግዛት እየተደረሰ ፣ ስም የፈረንጅ ካልሆነ የፉራ ተብሎ እየተቀየረና በዚያውም የፈረንጁን ትምህርት በድጎማም ሆኖ በአየር ባየር እንደነመለስም ቢሆን ተማርኩ ብሎ ወረቀት ያልያዘው ሁሉ አልሰለጠነም ተብሎ ባለበት ሁኔታ ትግልም ሆነ ሀገር የምርጦች ሳይሆኑ የጭቁኑ ሕዝብ መሆናቸውን ዳግም ማስረገጡ ሲያንስ ነው። ለምሁርነቱ ደግሞ ቀለም ከመንዳት ባሻገር በጭንቅላት በአንጎል መጠቀምን ማማልከቱን ካመንበት ከእነ እገሌ ዶክትሬት የማሚት ሰርቲፊኬት ይሻላል በሚያሰኝ ሁኔታ መደናቆርም ካባ ለብሶ ሊገኝ ይችላል፡፡ ምሁሮች በሀገር ወዳድነትና ህዝባዊነት ለሀገርና ለሕዝብ ያደረጉት አስተዋፅዖ የማይካድ ከመሆኑ ሌላ በተባለው የትምህርት ሂደት አልፈን የተወሰነ ዕውቀት የገበየነውም የአቅማችንን ለማድረግ ስንጥር መቆየታችን የሚካድ አይደለም፡፡ ሕይወታቸውን ለሕዝብ የሰዉት እነ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ኢንጂኔር ኦስማንና ሌሎች የኢሕአፓ ጀግኖች ሁሉ የተገቢው ምሁር ምሳሌ ናቸው። ታዲያ ምሁር ስንል ምሁር ሲሉ መባሉና መጠየቁና ለህዝብ የቆመውን ምሁር በህዝብ ላይ ከሚያላግጠው ምርጥ በሉኝ መለየቱ ተገቢ ነው ቢባል ምን ስህተት አለው? ትምህርት ከተባለ በደፈናው ደግ ነው ጥሩ ነው ገንቢ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ለምሳሌ አሁን ያለው የወያኔ የትምህርት ፕሮግራም ከወደ ማስተማሩ ሳይሆን ወደማደንቆሩ ጫን ይላል ተብሏል፡፡ መስመር የሳተ ትምህርት ወይም ፈረንጅ ካልተጠቀሰ ለሚሉት እንዲገባ ደግሞ ሚስኤድዩኬሽን የሚባለውም አለ። በትምህርት ሽፋን አንጎል አጠባ፡፡ ሀሰትን ሀቅ ብሎ ለማስጨበጥ፡፡ አፍሪካኖች በአጠቃላይና ኢትዮጵያውያንም ብንሆን የራሳችን ታሪክ ተዛብቶ ተምረናል፣ እንማራለንም፡፡ ይህ ትምህርት ሊባል አይችልም፡፡ ፊታችን ጥቁር፣ ጨምበላችን ነጭ ብሎ የተፃፈውን ያስታውሰናል፡፡ ጣሊያን ቅኝ ቢገዛን ይሻል ነበር ወደሚል መድምደሚያ ደርሶ ይህን ሊሰብክ የሚነሳ ምሁር (ይህን ብሎ መፅሀፍ የፃፈ አለና) ተብዬ ተማር ሊባል ነው? ታሪክ እየጎበጠና እየተበረዘ ራስን አዋርዶ በዝቅተኝነት ስሜት ራስን ለመሸቀብ መጠቀሚያ ሆኖ ለአፍሪቃውያን የዝቅተኝነት ስሜት መሰረት ሆኗል፡፡ ጠባብ ብሄርተኝነትስ መማርን ማወቅን ያመለክታል? ትምክህትና ዘረኝነትስ ያለመማርና የመደናቆር ምልክት አይደሉምን? መማር ማወቅ ከሆነ፣ ክፉና ደግን መለየት ከሆነ፣ ምሁር ለመባል መብቃቱ ካባ ለብሶ ወረቀት መቀበሉ ብቻ ሳይሆን የሀገርና የህዝብን ሁኔታ የሚረዳ ንቃት መገብየቱ ከሆነ በግልቡ “ፕሮፌሰሩ ያውቃሉ” ድምዳሜ ቦታ ሊኖረው አይችልም፡፡ በቀይ ሽብሩ ዶክተሮቹ የስንቱን ወጣት ገላ በእሳት አቃጥለዋል ፣ ስንቱን ረሽነዋል፡፡

ከዚህ ሌላ ደግሞ ዕውቀት ምንጩ ባዕድና ፈረንጅ ነው ተብሎ የሀገር ቅርስና  ዕውቀት ከተናቀ
መጨረሻው አያምርም። “ፈረንጁ እያሉ የምን የኢትዮጵያዊ አለቃ!” ብለው የሚገረሙ ይበራከ
ታሉ፡፡ ይህ ሁሉ በግንዛቤ ተይዞ ጉዞ ከተጀመረ እኛ ሰልጥነናል ባላገሩ ግን ፋራና ኋላ ቀር ነው የ
ሚለው የተሳሳተ ድምዳሜ ይሰፍናል፡፡ ባላገሩ ባለሀገር ባይሆንም በተመክሮውና ቅርሱ ከአያሌ ጥ
ራዝ ነጠቆች ብዙ ዕውቀት እንዳለው መታወቅ ያለበት ነው፡፡ በህብረተሰባችን የዴሞክራሲ ስርዓ
ትን ሊያዳብሩ የሚችሉ ባህሎች ተንፀባርቀ እንደነበርም፣ በሁሉም መስክ ህዝባችን የራሱ ስልጣኔ
ቅርስ እንዳለውም ማወቅ የተማረ ያሰኘናል፡፡ በፍልስፍና ዛሬ አንዴ ፕላቶ አንዴ ሆብስ እያሉ ሊ
ራቀቁብን የሚጥሩትን የእኛም ዘርዓያዕቆብ ነበር ብንላቸው ምን ያስቆጣል? የሚቀናበት ጠፍቶስ
ነው ዶክተር በተባለው ላይ ሁሉ የሚቀናው? ባህታዊ ገብረ ስላሴ በየካቲት 66 ሰሞን እውነቱ መ
ቸ ተነግሮ አልቆ ነው ውሸት የምጀምረው ያሉትን የሚያስታውስ ነው፡፡ እንቅና ካልን ለህዝብ አ
ገልጋይ በሆነው ምሁር ላይ መቅናቱ ያምራል፡፡

የሕዝብ ትግልን በተመለከተ ደግሞ ወደ ድል መጓዝ ከተፈለገ በሂደቱ ላይ የሚጋረጡትን ችግሮ
ች ሁሉ ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡ ውዝግንብሩ ተኖ በትግሉ ላይ ጥርት ያለ ግንዛቤ ሊሰፍን ካልቻ
ለሞኝ አሞራ ያባቱ ዋሻ ይጠፋዋል ሆነን አንዱን አረመኔ በሌላው ጨቋኝ እየተካን የመከራ ኑሮን
መሸከም እንገደዳለን፡፡ ሰው የተፈጠረው ለመሞት ሳይሆን ያለውን ጊዜ በደስታ ለመኖር ነው እስ
ካልን ድረስና በጨለምተኝነት ካባ እስካልተሸፈንን ድረስ አስከፊ የኑሮ ሁኔታችንን በትግል ለመለ
ወጥ መጣር መዋደቅ ግዴታችን ይሆናል፡፡ በመሆኑም ትግላችን ይሰምር ዘንድ፣ የምንከፍለው የ
ደም ዋጋ እንዳይበዛ፣ በደማችን ሌሎች እንዳይነግዱ፣ ለገሰን በለገሰ እንዳንተካ፣ በሀሳዊ መሲሆች
ና ፈሪሳውያን መደናገር የለብንም። ስለዚህም በአንድ በኩል ትግሉ የራሳችን ስለሆነ፣ የእኛው ጉ
ዳይና የሞት ሽረት ጥያቄያችን ስለሆነ ማንም በእኔ አውቅላችኋለሁ ለጉሞ ሊነዳን የሚችል ባለ
መሆኑ መሪዎች የተባሉት/ብዙዉን ጊዜ ያውም ያልመረጥናቸው/ በጣዖት ደረጃ ሊሰየሙብንና ከ
ትችታችን ነፃ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ለበሰበሰ ስርዓትና ለጨቋኝ አልገዛም ብሎ እየዘመረ ያመፀው
ትውልድ ቢያንስ በዚህ ዓይነቱ ስገዱልኝ፣ በጭፍን ታዘዙኝ፣ ሳይሰሩ አንቱ በሉኝና አፋችሁን ዝጉ
ፖለቲካ ሊሰማራ ከቶም የሚታሰብ አይሆንም፡፡ ፀሀዩ ንጉስንም ሆነ ሁሉን አዋቂ ነኝ ያለውን ኮለ
ኔል የታገለ ነውና ዛሬ በተራና ዘረኛ ግብዝ ሊደናገር አይችልም፣ መንጌ--መሌ ከአፉ ሊወጣ አይ
ጠበቅም።ስለዚህም የመተቸትና የመገሰፅ መብታችን የተከበረ  ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ህዝብ ነውና
፣ የትግሉ ባለቤት ህዝብ ነውና ድርጅቶችና መሪዎች ለሕዝብ ተገዢ መሆናቸውን መካዱ ትክክ
ል አይደለም፡፡ ራሳቸውን ከህዝብ በላይ አድርገው የሚፈርጁ ወይም ህዝብን ናቅ አድርገው ከአፍ
ዘጋ ከጆሮ ከፊት አድርጌህ ትዕዛዝ ተቀበል የሚሉቱ የሰለጠኑ ሳይሆኑ ልናስወግደው ከምንታገለ
ው እምብዛም ያልተለዩና ከህዝብ የተነጠሉ ናቸው፡፡ ትችት ከተባለ ደግሞ ነጋ ጠባ ኢሕአፓን ከ
ትችት አልፎ ሲዘልፉ የሚደመጡት ለምን ተተቸን ቢሉ አግባብ ያለው አይሆንም፡፡ ድርጅቶች
የየራሳቸውን ጥፋትና ድክምት መመርመር አለባቸው ሲባልም ሂስ ግለሂስን በራስ መዋረድ ደረጃ
የሚፈርጁ ካልሆኑ ሌሎቹ ይህን ቀና ምክር የሚቀበሉ መሆን አለባቸው፡፡ ኢሕአፓ ለምሳሌ ራሱ
ን ገምግሞ ጥፋቴ ያለውን ሲያምን በሌላ በኩል ደግሞ ባላጠፋው ለሚወነጅሉት ደግሞ የመከላከ
ያ ምላሹን ሰጥቷል፡፡ ለሂሱ አመስግናሁ ይላል እያለ ግን፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ በሌላ በኩል ደግሞ ትግላችን እንዲያቸንፍ እንፈልጋለንና ድክመታችንን መመ
ርመርና  እርምት መሻት ግዴታ ነው፡፡ በተቻለ መጠን ገበናን በአደባባይ አስጥቶ ለጠላት አለመ
መቸቱ ይመረጣል ግን ምስጢር የባቄላ ወፍጮ ሆኖ ጠላትንም ወዳጅንም እያደነቆረ ባለበት አት
ተቹ፣ ድክመትን አትመርምሩ ማለቱ ህዝብን ማፈን ይሆናል፡፡ በተለይም ምስጢር ተብዬው በወ
ያኔ ታውቆ እያለ ከህዝብ ይደበቅ ማለቱ አስተዛዛቢ ይሆናል። ከዚህ ግንዛቤ ስንነሳ  ዛሬ ሰለጠንኩ
ብሎ እዩኝ ተቀበሉኝ የሚለው ፖለቲካ ያልሰለጠነ፣ ለህዝብ ከቶም የማይበጅ፣ እንዲያውም ጉዳት
ያስከተለን ተመክሮ ሊደግም የተነሳ መሆኑን ጠቁሞ ማስጠንቀቂያ ደወልን ማቃጨል ግዴታችን
ይሆናል፡፡ በዚህ ላይ የግለሰቦች ቦታ ደግሞ ሲታይ በታሪክ አጋጣሚ የሚጫወቱት አሉታዊም ገን
ቢም ሚና ሊኖር ቢችልም ለተክለሰብ ግንባታ ቀዳሚ ቦታን እስካልሰጠን ድረስ ትግሉ እንጂ፣ ሀ
ገር እንጂ ግለሰቦች ዋና አይደሉም፡፡ የድርጅት መሪ ሊተች ሊወቀስ ይችላል ብቻ ሳይሆን ይገባ
ልም፡፡ ገና ከጠዋቱ ያውም በትግል እሳተ ፈተና ሳይታለፍ በጣዖት ደረጃ ግለሰቦችን አስቀምጦ አ
ምልኮት ስህተት ነው፡፡ ወደፊትም የሚያራምድ አይሆንም፡፡ ለዚህም ነው ትችት ሲደመጥ እንዴ
ትስ ደፈራችሁ ብቅ የሚለውና አፍ ለማዘጋት ዘመቻው የሚጧጧፈው፡፡ ከትግል ተመክሮ በአጠ
ቃላይ መልኩ በመነሳት መመርመሩ ተገቢ ቢሆንም በክስተቶች ዙሪያ ደግሞ ግለሰቦች ባላቸው
ሚና መጠቀሳቸው የማይቀር ነው፡፡ ትግሉን ከድተው ለወያኔ የሰገዱት ስማቸው መጠቀሱ ትምህ
ርታዊ ነው--ታሪካቸው እንዲታወቅ፡፡ የሕዝብን የሙት ከተማ አድማ ተፎሩጠው አክሽፈው ከፀ

ረ ኢትዮጵያዋ ፈረንጅ ጋር ፎቶ የተነሱት ሁለቱም ሰዎች ስማቸው መነገሩ ተገቢ ነው፡፡ ጅብ የ
ማያውቁት ሀገር ሄዶ ቆዳ አንጥፉልኝ እንዳይል፡፡

ከዚህም ስንነሳ ስለፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች ግንዛቤያችን የተስተካካለ መሆን አለበት፡፡
ፖለቲካ ድርጅቶች የሚከሰቱት በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የተነሳ ነው፡፡ ድርጅ
ቶች ከመደብ በላይ ሳይሆኑ  የህብረተሰቡን ክፍሎች የአንዱን ወይም የሌላውን ጥቅም ለማስጠበ
ቅ የሚነሱ ናቸው። ለሰራተኛው ቆመናል ብለው ለከበርቴው የቆሙ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ለዴሞክራስ
ˌመጣን ብለው አምባገነኖች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሁሉም ግን ሚናና የየራሳቸው ድጋፍና ሰልፍ አላቸ
ው፡፡ ከዚህ ውጪ የሚሆን ድርጅት የለም፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ድርጅቶች የህብረተሰቡ  ፍሬ እን
ደመሆናቸው መጠን ያሉበት ተጨባጭ ሁኔታና የህብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ ተፅዕኖ ያደርግባቸ
ዋል፡፡ ከአባሎቻቸውና መሪዎቻቸው ይዘት ደግሞ ጠባያቸውና የራሳቸውም ሁኔታ ይቃኛል፡፡ በ
መሆኑም ከልዩ ልዩ ድክመቶች ነፃ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ምንኛ ሰለጠንን ወይም ዘመናዊ ሆንን ቢ
ሉ ኋላ ቀርነትንም አቅፈው ሊያንፀባርቁ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ በኢሕአፓ ተመክሮ ራሱ ከኢሕአ
ፓ ህዝባዊና አብዮታዊ አቅዋም ውጪ አቅዋም የያዙ ግን የድርጅቱ አባላት የሆኑ እንደነበሩ ለ
መገንዘብ ተችሏል፡፡ አስመሳይ ተራማጅ ይባሉ የነበሩ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ድርጅቶች እርስ በ
ርስም ሆነ በውስጣቸው መከፋፈላቸው የሚጠበቅ ሊሆን ይገባዋል። ባይሆን ኖሮ ደግ ግን አይቀ
ሬ ነው ማለቱ የተሻለ ነው፡፡ በድርጀቶች መሀል የማይታረቅ ቅራኔ ሊኖር ይችላል--እንደ ሰልፉ
ቸውና አቅዋማቸው፡፡ ለምሳሌ በወያኔና በኢሕአፓ መሀል ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ ነበርና ለግ
ጭት በር ከፍቷል፡፡ መኢሶንና ኢሕአፓም ቅራኔያቸውን ሊያረግቡ ስላልቻሉ እንዲሁ ሊጋጩ ች
ለዋል፡፡ በኢማሌድህ የነበሩትን ሰደድ በልቷቸዋል፡፡ የፖለቲካ መስመር ልዩነት ሲከሰትም ለክፍፍ
ል በር ይከፍታል፡፡ ይህን ልዩነት በአግባብ ፈቶ መቀጠል ይቻላል አይቻልም ሌላ ከአየያዝም በላ
ይ የሆነ ጥያቄ ነው፡፡ የግለሰቦች አለመጣጣም ወይም የስልጣን ጥም ልዩነትንም ሊያመጣ ይችላል
፡፡ በአጭሩ ድርጀቶች ሊከፋፈሉ፤ ሊጋጩም ይችላሉ፤ ያለና መጠበቅ ያለበትም ነው፡፡ ዋናው የ
ሚመለከተን ቁም ነገር ግን በአንድ ጎራ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች በተወሰነ ደረጃ የፕሮግራም ልዩነ
ት ቢኖራቸውም ይህን አቻችለው በዋናው ጠላት ላይ ማተኮር አለባቸው የሚለው ነው፡፡ የቅራኔ
አፈረጃጀትና አያያዝ ችሎታን ይጠቅሳል፡፡

በነበረው ሂደት ተደጋግሞ ያየነው በሀገራችን የፖለቲካ መሬት ድርጅቶች ብቅ ሲሉ በራሳቸው
ፕሮግራም መሰረት ድጋፍን ከመሻት ይልቅ የነበሩትን በማውገዝና በማጫጫት ሊጠናከሩ ስለሚ
ፈልጉ ቅራኔዎች ወድያውኑ ይከሰታሉ፡፡ ጥፉ የሚባሉት ለምን ብለው የመከላከል እርምጃ ይወስ
ዳሉ፡፡ አዲስ የመጡት ደግሞ ያለፈውን ተመክሮ በቂ ቦታ ስለማይሰጡ በደም ከተገበየው ዕውቀ
ት መማር ተስኗቸው ስህተቶችን መድገም ይገደዳሉ፡፡ በመሰረቱ በፀረ ወያኔው ትግል የተሰማሩና
ኢትዮጵያዊ የሆኑ ድርጀቶች ያብሩ ዘንድ የሚያግድ ትልቅ እንቅፋት መኖር እንደሌለበት የሚ
ታይ ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ድርጅቶች ከወያኔ ወይም ከአገዛዙ በላይና በፊት ጠላታቸው ሌላ ፀረ
ወያኔ ድርጅት ይሆናል፡፡ ኢሕአፓ ስልጣን ከሚመጣ ወያኔ በስልጣን ይቀጥል ያለው የተቃዋሚ
ቡድን መሪ ነኝ ባዩ ሰው በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ድርጅቶች ለፖለቲካ ስልጣን የሚታገሉ ቢ
ሆንም ቢያንስ በኢሕአፓ አመለካከት ያለው ፀረ ህዝብ አገዛዝ እስከተወገደ ድረስና አሸናፊው ማ
ንም ይሁን ማን የዴሞክራሲ መብቶችን እስካከበረ ድረስ ኢሕአፓ በሀገሩ በይፋ ወጥቶ ለመታገል
ዕድል ይኖረዋልና ለምን እኔ በቅድሚያ ስልጣን አልመጣሁም የሚል ባለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ
ያለው አመለካከትና አቅዋም የተለየ ነው፡፡ ይህንንም ደጋግሞ ገልጧል፡፡ ድርጅቶች መፎካከር ያ
ለባቸው ማን ለስልጣን መጀመሪያ በሚለው ሳይሆን ማን በስፋት ህዝብን አሰባስቦ በቆራጥነት ወ
ያኔን ይታገላል ፤ ያታግላል በሚለው ላይ መሆን አለበት፡፡ የስልጣን ሹክቻው አሉታዊ ፉክክርን
ና ግጭትንም፤ አንዱ ለሌላው ጋሬጣ መሆንን ያስከትላል፡፡ ለመታገልና ለማታጋል ግንባርቀደም
ለመሆን ፉክክሩ ግን ትግል ያጎለብታል፡፡ ለዚህም ነው በሁሉም የህብረት ጥረቶች ኢሕአፓ ከሌለ
ˌች ጋር በእኩልነት ተሰልፎ የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማድረግ ሲጥር የቆየው።

የድርጅቶች ዕድሜና ተመክሮ የቅደም ተከተል ጉዳይ ሆኖ ሳለ የቆየውን መጤው ሲያወግዘው ወ
ይም ዕድሜ ብዙው አዲሶቹን ሲንቅ ማየቱ ደግሞ ድክመት መስፈኑን የሚጠቁም ነው፡፡ በኢዴኅ
ጎ ምስረታ ተስፋ ያደረገ ዜጋ ብዙ ነበር-- ያ ግን ሳይውል ሳያድር ተደናቀፈ። ለምን ብሎ መመ
ርመሩና ያጠፋውንም መውቀሱ ተገቢ ነው። ለድል የደረሰው የህዝብ ትግል ተደናቀፈ--ለዚህ ም
ክንያቱ አንደኛው የገዢ ቡድን አፈና ቢሆንም የተቃዋሚዎችም ስህተቶች የራሳቸው አስተዋፅዖ
አድርገዋል፡፡ ስህተትን ላለመድገም ይህን መመርመሩ ለምን ይከለከላል? ድርጅትን ወይም የድር
ጅት መሪዎችን ወይም መሪን ፍፁም አድርጎ መውሰድ ጎጂ ስህተት መሆኑ እየታወቀ ለምን እን

ደቀና አቅዋም ተደርጎ ይሰበካል? ቃለ አጋኖ ፖለቲካ በሚለው ላሳስብ እንደሞከርኩት የሆነ ድር
ጅትን አወድሶ ከእሱ ሌላ ላፈር ማለቱ፣ የሆነ መሪን ደግሞ ሰማይ ሰቅሎ መወድስ መደርደሩ እ
ውነቱን ወደ መዘንጋቱ መጓዙ ስህተት ከመሆኑ በላይ ትግልን ይጎዳል:: ብዙዎች በገንቢ ሂስና ት
ችት፣ በስድብና ዘለፋ መሀል ያለውን ልዩነት ይስታሉ:: ድክመቶች ተከስተው ትግሉ ሲጎዳ ይህን
ለማረም መነሳትና ስህተተን በቀና መንፈስ መጠቆም ስድብም ጎጂም አይደለም:: ራቁቱን ቆሞ
ካባ ለብሼ,ያለሁ ለሚል ልብስ የለህም ማለቱ አስፈላጊ ነው:: ዛሬ በየፓልቶኩና ድህረ ገፆቹ እንደ
ምንታዘበው ግን መተቸትና መውቀስ በሚል የሚደመጠው መዘርጠጥና መሳደብ (በኢሕአፓ፣በሰ
ማዕቱና በመሪዎቹ ላይ ለምሳሌ እየተካሄደ ያለው) ገንቢ ሳይሆን አፍራሽ ነው:: ውይይትን ወደ
ፊት አያራምድም፣ ለመሻሻል ጥቆማን አያቀርብም። ከቃለ አጋኖና ጭፍን ስድብ ና ውግዘት ፅን
ፎች እንቆጠብ ስንል ወይም ተምረናል ሰልጥነናል በሚል ህዝብን አንናቅ ስንል ቀና ጥቆማና ም
ክርን ለማካፈል እንጂ ለሌላ አለመሆኑም ግልፅ መሆንም ነበረበት:: ድርጅቶች በወንድሜ ግንባር
ደም አልይበት ይባባሉ ስንል አንዱ ሌላውን እየፈነከተ ወንድሜን ወንድሜን ግን ያነብንብ በሚ
ል አይደለም::

ድርጅቶች ከተቻለ ልዩነትን በውስጣቸው ይዘው ቢፈቱ ይመረጣል ብንልም ይህ ሁሌ ሊሆን እን
ደማይችልና ክፍፍልም ተከስቶ ጉዳት እንደሚመጣ የታወቀ ነው:: በበኩላችን ልዩነት ሲመጣ ገበ
ና በውስጥ ተይዞ ሊፈታ ቢሞከር ይሻላል ብለን አሳስበናል:: ከህዝብ ጎራ ማንኛውም ድርጅት መ
ከፋፈሉ ለትግሉ ጠቃሚ አይደለም:: ይህ ክፍፍል ግን የራሱ ምክንያቶች እያሉት ችግሩን በሌሎ
ች ላይ በመጣል ሌሎችን መወንጀል መምረጡ ደግሞ ችግሩን ይበልጥ ያባብሰዋል:: ህብረት እን
ደተቋቋመ ያጋጠመው ችግር በኢሕአፓ የተፈጠረ አይደለም። ቅንጅት እንደ ድርጅት ትላንት
ም ሆነ ዛሬ የተከሰተበት ችግር ጋር ኢሕአፓ ቅንጣትም ግንኙነት የለውም። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግ
ን በኢሕአፓ ላይ የቅንጅት አንደኛው ክፍል ይሁነኝ ብሎና ወስኖ ዘመቻ መክፈቱ፣ በፅሁፎችና
በድህረ ገፆችና ፓልቶክ መድረኮችም በኢሕአፓ ላይ ማዘመቱ የሚታወቅ ነው:: ይህ መቆም ያለ
በት ከመሆኑ ባሻገር ተለያየን የሚሉትም ክፍሎች ሁሉ የህዝብን ቃል ኪዳን ተፃርረው ጎራ እስካ
ልቀየሩ ድረስ የትኩረታቸው አቅጣጫ የመለስ አገዛዝ እንዲሆን ማሳሰቡ ወቅታዊ ነው። ከዚህ ሌ
ላ ግን ማንኛውም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተደቀነን አደጋ ማጋለጥና መታገልም የኢሕአፓም የ
ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋም ግዴታ በመሆኑ ትችቱ እነ እገሌን ያስቀይም ይሆናል በሚል በዝምታ
መታለፍ የለበትም:: ማንኛውም ድርጅት በወሰነውና ባመቸው መሰለፍ ሆነ መጓዝ መብቱ ቢሆን
ም መንገዱ ለትግል የማይበጅ እስከሆነ ድረስ ተቃውሞ የማሰማት መብት በማንም ሊታገድ አይ
ችልም:: ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ወይም ኤኤፍዲ የተባለው ስብስብ ሲመሰረት ህብረቱ ለ
ምን ይህ ስብስብ ከመነሻው ጀምሮ የማይበጅ መሆኑን አስረድቶ አቅዋም መያዙና ይህንኑም ማሰ
ማቱ ተገቢና ግዴታውም ነበር:: በአሁኑ ወቅት ማንኛውም ድርጅት ከመለስ አገዛዝ ጋር በጠረጴ
ዛ ዙሪያ በአዲስ አበባም ሆነ በአትላንታ ተሰብስበንና ተስማምተን በመጪው የመለስ የምርጫ ቲ
ያትር አጃቢ ተዋንያን እንሁን ሊል ቢነሳ መቃወም መብታችን ብቻ ሳይሆን ትግሉ የሚጠይቀን
ግዴታ ነው:: ስህተት ተደግሞ ትግል እንደገና መቀመቅ ሲወርድ ማየት የለብንምና ። የሰማዕት
ን ደም ረግጦ ከነፍሰ ገዳዩ ቡድን ጋር በሆነው መንገድና ደረጃ ለመተቃቀፍ መነሳቱ፣ ውሳኔያቸ
ው ሲጎዳን ለከረመ ባዕዳን ዳግም ጆሮ ሰጥቶ ትግልን ዳግም ለመለስ ሰለባ ለማቅረብ መዘጋጀቱ ከ
ስህተትም አልፎ ትግሉ ላይ ወንጀል ሊባል ይገባዋል ብንል ቃለ አጋኖነት አይሆንብንም:: ትግሉ
ከግለሰቦችና ድርጅቶች በላይ ነውና፣ የህዝብ ነውና የመጀመሪያ ጭንቀታችን ለህዝብ ትግል መ
ጠንከር እንጂ ለሌላ አለመሆኑ በገቢር መታየት ያለበት ነው::

የትግሉም ሆነ የሀገር ባለቤት ህዝብ እንጂ ማንም ምርጥ ነኝ ባይ ግለሰብ ወይም ቡድን አይደለም
ስንልም ይህ የሆነን ሰው ወይም ስብስብ ለማጥቃት ሳይሆን ሀቁን ለማስረገጥ ነው:: ይህን ሀቅ መ
ድገም ያስገደደን ተመክሮ ደግሞ ጥቂቶች የህዝብ ድል ሲነጥቁ በ67ም በ83ም ስላጋጠመን ብቻ
ሳይሆን ዛሬም የሀገሪቷ ፖለቲካ በምርጦች ይወሰን ባዮች በመድረክ ስላሉ መሆኑ መታወቅ አለበ
ት:: የኢትዮጵያ ህዝብ ላቡን አንጠፍጥፎ ያስተማራቸው ልጆቹ ምስጋናቸው፣ ውለታውን መክፈ
ላቸው አገልጋዩ በመሆን፣ ለደህንነቱና ለመብቱ መቆም መከሰት ሲገባው ተማርን ብለው ባስተማ
ራቸው ህዝብ ላይ ሊኮሩ ከተነሱ ኩራት አስጠየፊ ለብሶ ድንቁርና ማለቱ ሲያንስ ነው:: ቀደም ተ
ብሎ ተገልጦ እንደነበረው ህዝባችን ቢደኸይም፣ ጮማው የዱባ ሰንጋ ቢሆንም፣ ቢታረዝ ቢራብ
ም፣ የባዕድ ቋንቋ ባይናገርም፣ ወደ ባዕድ ሀገር በነቂስ ተነስቶ ባይፈልስም የሀገሩ ባለቤት፣ ባለሀገ
ር ነውና የዚችን ባለታሪክ ሀገር ቅርስ በመዳፉ የያዘ አዋቂ ህዝብ ነው። ማንም ሊንቀው ወይም የ
ነገ ዕጣውንና የሀገሩን ሁኔታ ከመወሰን ሊያገለው አይችልም:: ሀይል የህዝብ ነው ስንል ቢያንስ በ
ኢሕአፓ የሚታመንበት እንጂ ለይስሙላ የሚነገር አይደለም:: ምሁራን ለህዝብ አጋልጋይ በመ

ሆን፣ ትሁትነትን ተላብሰው፣ ሳይኩራሩ፣ በቀል ብቻ ሳይሆን በገቢር ለትግል ከቆሙ፣ በሁሉም መ
ስክ ታጋይ አለና ዘፋኙም፣ ደራሲውም፣ አስተማሪውም፣ ፈላስፋውም፣ ካህኑም ሼኩም ሁሉም የህ
በረተሰቡ አካል ለትግል ካለው አቅዋም አንፃር ይፈረጃል:: ከስሙ በፊት ቅፅል በመለጠፉ ብቻ ሳ
ይሆን:: ምሁር የሚከበረው፣ ታጋይ ነኝ የሚል ሁሉ የሚከበረው በተጨባጭ ሲታገል ነው:: በዛሬ
ው ተጨባጭ ሁኔታ ፀረ ወያኔ ያልሆነ ምሁር ሊከበር አይገባውም:: የድርጅት መሪ ሊሆኑ የሚገ
ባቸው ለወያኔ የሚለሰልሱ፣ ለባዕዱ አመቺ መስለው የሚታዩና በፈረንጅ የሚወደዱ ሳይሆኑ ለወ
ያኔና ሀገራችንን ለሚጠሉ ባዕዳን የሚጎረብጡ ጀግና ኢትዮጵያውያን መሆን አለባቸው:: ወያኔን
ወዳጅ የሚልና ህዝብን የሚንቅ ምሁር ሊባል አይገባውም:: ህሊናውን ቀስቅሶ ገና መማር ማወቅ
ና መስተካከል ያለበት ነው:: ባለፈው የትግል ሂደት አወቅን ያሉቱ አንድም በአገዛዙ ላይ ብዥታ
ን ይዘው በሌላ በኩል ደግሞ ለባዕድ አመቺና ቀላል ሰለባ ሆነው ከመገኘታቸው ሌላ ከመደራጀት
ና በዘላቂው ከማደራጀት አንፃር ደግሞ ድክመት እንደነበራቸውና በመሰሪው ወያኔ ሊጠቁ እንደ
ቻሉ አይተናል:: የሰለጠነ ፖለቲካ አባወራ ነን ብሎ ለመኩራራት ጊዜው ካለመሆኑ ሌላ ፖለቲካ
ዉ ራሱ ህዝባዊ አልሆን ብሎ በአጠያያቂነት እየተተቸ መሆኑንም መዘንጋት አይገባም:: አፍን
ሞልቶ ወያኔን ጠላት ማለት አለመቻልና መለሳለሱ ዕውቀትም፣ ስልጣኔም፣ ለትግሉም የሚጠቅ
ም ፖለቲካ አይደለም:: የመለስ አገዛዝ የህዝብም የሀገርም ዋና ጠላት ነው:: ከዚህ ሌላ ቅራኔ አፈ
ረጃጀት ለውድቀት ማለትም ትክክል ነው::

የመለስ አገዛዝ በዚህም በዚያም ብሎ በስልጣን ለመቀጠል ከቻለ ጀምሮ ተቃዋሚዎችን ለማውደ
ምና ካልቻለም ለመከፋፈል ቆርጦ እየተንቀሳቀሰ ነው:: በዚህም ዘመቻው ሀያል መንግስት ነኝ ባ
ዩ ባዕድ እየተባበረው ነው። የፖለቲካ ሀይሎች እርስ በርስ ተባብረው ትግሉን እንዳያፋፍሙ ሰር
ጎ ገቦችም ሆኑ ባዕዶቹ ክፍፍልን እያራገቡ ነው:: በተወሰነ ደረጃ ውጤት ማግኘታቸውም ዛሬ ይ
ታያል:: ድክመቱ ያለው በመሪዎች ዘንድ እንጂ በተመሪዎች በኩል አለመሆኑ ደግሞ ዛሬ ክርክር
ን አይጋብዝም:: ውጣ ተሰለፍ ሲሉት የሚሰለፍና የሚገደል፣ አፈናን ጥሶ ወኪሎቹን የመረጠ ፣
ለአድማ ዝግጁነቱን ያሳየ፣ አድማውን አጥፈነዋል ሲሉትም የተቀበለ ወዘተ ለትግል የተነሳሳ አ
ግባብ የሌለውንም አመራር ሊቀበል የተዘጋጀ ህዝብ ሆኖ ሳለ ደክሞ የተገኘው ክፍል መሪ ነኝ ያ
ለው ነው:: ይህን ማለት ደግሞ የህዝብ ጎራን ምስጢር ማባከን አይደለም:: በፖለቲካው መድረክ
ና በተቃዋሚዎች ጎራ ግንባር ቀደም ነን ያሉት ሁሉ ህዝብን ትግል ሊመሩ ሆነ በፅናት ፀረ ወያኔ
ውን ትግል ሊወክሉ መቻላቸው አጠራጣሪ ነው:: ይህም መነገርና መታረም አለበት:: ዛሬም ቢሆ
ን ፀረ ወያኔ የሆኑት፣ ይህ አገዛዝ መውደቅ አለበት የሚሉት፣ ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙት፣ ለ
መስዋዕትነት ዝግጁ የሆኑት ሀይሎች ማበር መተባበር አለባቸው:: ትላንትም ውድቅና ትግል አጥ
ፊ መሆኑ በገቢር የታየው ለወያኔ እጅ የመስጠቱ አቅዋምና ፖለቲካ ዛሬም ተቆነጃጅቶ ወይም
ጨምበል አጥልቆ ቢመጣ ሌላ ውጤት የለውምና መወገድ ያለበት ነው:: ጠላትና ወዳጅን መለየ
ት፣ ጠላታችን የመለስ አገዛዝ መወገድ እንዳለበት ማመን፣ ለባዕድ አለመጎንበስና ህዝብን አደራጅ
ቶ ለወሳኙ ድል ማታገል ያስፈልጋል:: ለዚህ ትግል ጠቃሚና አቅጣጫ ሰጪ የሆነ ተመክሮ አለ ፡
፡ የሚታገልና የሚያኮራ፣ ጠላቱን ያወቀ፣ሀገሩን የሚወድ ህዝብ አለ ፡፡ ድርጅቶች ተባብረው የመ
ሪውን ቦታ መያዝ ነው ያቃታቸው:: የሰለጠነ ፖለቲካ የሚባለውይህንን ድክመት ተገንዝቦ ለማስ
ወገድ የሚጥረው ነው:: ለመለስ አገዛዝ መስገዱማ፣ ለሰሞነኛ ግራዚያኒ መንበርከክማ ምኑ አዲስ፣
ምኑ ዕውቀት፣ ምኑ ብልህነት ሆኖ?

ተስፋ መቁረጥ ድንቁርና ካልተባለ ምን ሊባል ነው? ለጨቋኝ እጅ ሰጥቶ መገዛት አሳፋሪ ካልሆነ
ምን ሊባል ነው? ድክመታችንንስ መርምረን ካላስወገደን በምን ልንታረም ነው? ሀቀኛ የኢትዮጵ
ያ ልጆች አብረውና ተባብረው ካልታገሉ ድልስ እንዴት ይገኛል?

የትግልም የሀገርም ባለቤት ጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነው!!